Paid Leave Oregon

# አጠቃላይ እይታ

## ቤተሰቦቻችን፣ ጤናችን እና ደህንነታችን ላይ ተፅእኖ ለሚያሳድሩ አንዳንድ ወሳኝ የህይወት ጊዜያት በኦሪገን ውስጥ ያሉ ሰራተኞች ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ እንዲወስዱ የሚያስችል አዲስ ፕሮግራም።

**የቤተሰብ ፈቃድ -** ከባድ ህመም ወይም ጉዳት ላጋጠመው የቤተሰብ አባል እንክብካቤ ለማድረግ ወይም ከወሊድ፣ ጉዲፈቻ ወይም የማደጎ እንክብካቤ ምደባ በኋላ ከአዲስ ህፃን ጋር ለመላመድ።

**የሕመም ፈቃድ -** አንድ ሰው ከባድ የጤና ችግር በሚያጋጥመው ጊዜ።

**የደህንነት ፈቃድ -** ለጾታዊ ጥቃት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም የማሳደድ ተጠቂዎች።

## ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም መቼ ይጀመራል?

አሰሪዎች የደመወዝ መዋጮዎቻቸውን በጃንዋሪ 2023 የሚጀምሩ ሲሆን፣ ሰራተኞች ደግሞ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ማመልከት የሚችሉት በሴፕቴምበር 2023 ውስጥ ነው።

## ጥቅማ ጥቅሞች�:-

- በአንድ የጥቅማ ጥቅም መክፈያ ዓመት ውስጥ እስከ 12 ሳምንት የሚደርስ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ (እስከ 14 ሳምንት የእርግዝና ጊዜ- ተያያዥ የሕመም ፈቃድ)። አንድ ሙሉ ሳምንት ፈቃድ መውሰድ ወይም በተለያየ ጊዜ አንድ አንድ ቀን መውሰድ ይቻላል።
- በአሰሪዎ ድርጅት ውስጥ ከ90 ቀናት በላይ ሰርተው ከሆነ፣ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድዎን በሚጠቀሙበት ጊዜ ስራዎ የተጠበቀና ከስጋት ነጻ ይሆናል። ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ በመጠቀምዎ ምክንያት አሰሪዎ ሊቀጣዎ አይችልም።
- የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች የሚወሰኑት የእርስዎ ደመወዝ እና/ወይም ገቢ በግዛት አቀፍ ደረጃ ከሚሰጥ አማካይ ሳምንታዊ ደመወዝ ጋር ሲነጻጸር በሚገኘው ውጤት መሰረት ነው፤ በርካታ ሰዎች 100% የደመወዝ ምትክ ያገኛሉ።

## ሽፋን የሚደረግለት ማን ነው?

ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ከመጠየቁ በፊት ባለው ዓመት ውስጥ ቢያንስ $1,000 ያገኘ ማንኛውም ሰራተኛ ብቁ ሊሆን ይችላል። ኦሪገን ውስጥ የሚሰሩ አብዛኞቹ ሰራተኞች ሽፋን ይሰጣቸዋል። የጎሳ መንግስታት፣ ራሳቸውን ቀጥረው የሚያሰሩ የቢዝነስ ባለቤቶች፣ እና የግል ስራ ተቋራጮች ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራምን በማሳወቅ ለመሳተፍ መወሰን ይችላሉ።

## ወጪው የሚሸፈነው እንዴት ነው?

የሚከፈልበት እረፍት አሰሪዎች እና ሰራተኞች የሚከፍሉበት ፕሮግራም ነው። የኦሪጎን የቅጥር መምሪያ በየአመቱ እስከ ኖቬምበር 15 ድረስ የአስተዋጽኦ ዋጋን ወስኗል እና ይህም የሰራተኞችን ጠቅላላ ደሞዝ 1% የማይበልጥ ይሆናል።

የኦሪጎን አሰሪዎች ከክፍያ ጋር ለሚሰጥ ፈቃድ የትረስት ፈንድ መዋጮ ማድረግ የሚጀምሩት በጃንዋሪ 1/2023 ነው። መጠኑ አንዴ ከተወሰነ፣ ግዙፍ የሆኑ አሰሪዎች 40% የሚያዋጡ ሲሆን ሰራተኞች ደግሞ የእያንዳንዱን ግለሰብ አጠቃላይ መዋጮ 60% ያዋጣሉ ይህም ለ2023 1% ይሆናል። ከ25 ሰራተኛ በታች ያላቸው አነስተኛ አሰሪዎች ግን መዋጮ የማድረግ ግዴታ የለባቸውም። ይሁን እንጂ፣ 40% ድርሻቸውን ለመክፈል ለሚወስኑት የሚሰጥ ስጦታ ይኖራል።

## ተመጣጣኝ እቅዶች

አሰሪዎች ለሰራተኞቻቸው የራሳቸውን የሚከፈልበት የእረፍት እቅድ ለማቅረብ ሊመርጡ ይችላሉ። እነዚህ ዕቅዶች በስቴት ከሚተገበረው ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ጥቅማ ጥቅሞች እኩል ወይም የበለጠ የሚያቀርቡ መሆን አለባቸው፤ ሰራተኞችም የሚያደርጉት መዋጮ ከግዛቱ ዕቅድ መብለጥ የለበትም። የኦሪጎን ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ፕሮግራም ሁሉንም የአሰሪዎችን ተመጣጣኝ ዕቅዶች ማፅደቅ አለበት። አሰሪዎች ለተመጣጣኝ ዕቅዶች ማመልከቻቸውን ሴፕቴምበር 2022 ጀምሮ ማቅረብ መጀመር ይችላሉ።

## ይሳተፉ

ለሁሉም የኦሪጎን ነዋሪዎች ተስማሚ የሆነ ፕሮግራም መገንባት እንፈልጋለን። በሕዝባዊ ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ወይም አስተያየቶችዎን እንዲልኩልን ጋብዘንዎታል። ለበለጠ መረጃ የእኛን ከክፍያ ጋር የሚሰጥ ፈቃድ ድረ ገጽ ይጎብኙ።

## ተጨማሪ ይወቁ

የ paidleave.oregon.gov ይጎብኙ እና ለ*ኢ ሜይል ዝመናዎች ሰብስክራይብ*

*ያድርጉ*። በዚህ ኢሜይል ያድርጉልን paidleave@oregon.gov።

በስልክ ቁጥር 503-370-5800 ይደውሉልን።